*<u>በጣም የተራበ ሰው ምግብ ቤት ከገባ በኋላ፤</u>*

አስተናጋጅ፤ አቤት ጌታዬ፣ ምን ልታዘዝ?
ተስተናጋጅ፤ በጣም እርቦኛልና ፈጣን ክትፎ ብታመጣልኝ ደስ ይለኛል።

አስተናጋጅ፤ እሺ ጌታዬ፣ ለብ ለብ ወይንስ ጥሬ?
ተስተናጋጅ፤ ያው የሚፈጥነውን ጥሬ።

አስተናጋጅ፤ እሺ፣ በጣባ ወይንስ በሰሃን?
ተስተናጋጅ፤ የተገኘው ላይ።

አስተናጋጅ፤ እሺ፣ ማንኪያስ? የቀንድ ወይንስ የብረት?
ተስተናጋጅ፤ እንዴ ነፍሱ! በጣም እርቦኛል እያልኩህ? ማንኪያው ይቅር።

አስተናጋጅ፤ እሺ፣ በዳቦ ወይንስ በቆጮ?
ተስተናጋጅ፤ አንተ! በል አሳልፈኝ መሄዴ ነው።

አስተናጋጅ፤ በታክሲ ወይንስ በእግር?
ተስተናጋጅ፤ እንዴ! አንተ አፍንጫህን እንዳልልህ!

አስተናጋጅ፤ በጫማ ወይንስ በጥፊ?

ብለው ክትፎ አምጣ፣
አስተናጋጅ ለማጣ፣
ይህን ሁሉ ጣጣ፣
አስቲ ምን አመጣ፣
አምሮቴን ላልወጣ፣
ምነው በቀረብኝ አንጀቴ ቋጥሬ እዚህ ቤት ባልመጣ።